
# የአዲስ ኪዳን መቅድም




## መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ

**በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ**
**መንፈሳዊ ኮሌጅ**
**የሃይማኖት መምህር**

1977 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

## ቁጥር - ፩

# የሐዲስ ኪዳን መቅድም

## ክፍል 1 ጠቅላላ የሐዲስ ኪዳን መቅድም

### ምዕራፍ 1 ቅዱስ መጽሐፍ

1. የቃሉ ትርጉም
2. ቅዱስ መጽሐፍ የአምላክ ስጦታ መሆኑ
3. የ2ቱ ኪዳናት ግንኙነት
4. የቅዱስ መጽሐፍ መቅድም ዓላማው
5. የቅዱስ መጽሐፍ መቅድም አከፋፈሉ

### ምዕራፍ 2 ቀኖና ሐዲስ ኪዳን

1. የቀኖና ትርጉም
2. የቀኖናው መለያው ዘዴ
3. ከቀኖና ውጭ የሆኑ መጻሕፍት

### ምዕራፍ 3 አፓክሪፋ /ኅቡዓት/ ወንጌሎች

### ምዕራፍ 4 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መዝገቦች /ኮንዴክሶች/

1. ግሪክኛ የእጅ ጽሑፎች ሐዲስ ኪዳን
2. ጥንታዊያን ትርጉሞች በሐዲስ ኪዳን
3. የቤተ ክርስቲያን አባቶች የእጅ ጽሑፍ

### ምዕራፍ 5 የሐዲስ ኪዳን ቋንቋ

1. ኪኒ ዲያሌክት

## ክፍል 2. ልዩ መቅድም

### ምዕራፍ 1. ቅዱስ ወንጌል /ኢቫንጌሊዮን/

### ምዕራፍ 2. የወንጌላት እውነተኛነት

### ምዕራፍ 3. የማቴዎስ ወንጌል

1. ጸሐፊው
2. የመጽሐፉ እውነተኛነት
3. መቼ ተጻፈ
4. የመጽሐፉ ዓላማ
5. የመጽሐፉ የተለየ ጠባይ

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 4. የማርቆስ ወንጌል

1. ጸሐፊው
2. የመጽሐፉ እውነተኛነት
3. መቼ ተጻፈ
4. የመጽሐፉ ዓላማ
5. የመጽሐፉ የተለየ ጠባይ

## ምዕራፍ 5. የሉቃስ ወንጌል

1. ጸሐፊው
2. የመጽሐፉ ዓላማ
3. የጸሐፉ ምንጭ
4. መቼ የት ተጻፈ
5. የመጽሐፉ እውነተኛነት
6. የመጽሐፉ የተለየ ጠባይ

## ምዕራፍ 6. የዮሐንስ ወንጌል

1. ጸሐፊው
2. የመጽሐፉ እውነተኛነት
3. መቼ ተጻፈ
4. የመጽሐፉ ዓላማ
5. የመጽሐፉ የተለየ ጠባይ

## ምዕራፍ 7. የሲኖፕቲክ የመወራረስ /የመቀዳዳት/ ፕሮብሌም

1. በዘኅበሩ
2. በዘተለዩ

## ምዕራፍ 8. የሐዋርያት ሥራ

1. ጸሐፊው
2. የመጽሐፉ ዓላማ
3. የመጽሐፉ እውነተኛነት
4. መቼ የት ተጻፈ
5. የመጽሐፉ የተለየ ጠባይ

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል 3. የሐዲስ ኪዳን የትምህርት መጻሕፍት

### ምዕራፍ 1. መልእክታት

1. የመልእክታት ሐተታ
2. ቅ.ጳውሎስ ከተወለደበት ለወንጌል ትም/ስከ ተጠራበት
3. ቅዱስ ጳውሎስ በተአምራት እንደተመለሰ
4. የቅዱስ ጳውሎስ የስብከት ዘዴ
5. " " ሐዋርያዊ ጉዞ
6. " " በሮማ
7. " " መልእክታት

### ምዕራፍ 2. ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

1. ሀገሯ
2. የመልእክቱ ተቀባዮች
3. ወዴት መቼ ለምን እንደተጻፈች
4. የመልእክቱ እውነተኛነት

### ምዕራፍ 3. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ

1. ሀገሯ
2. ወዴት መቼ ለምን እንደተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

### ምዕራፍ 4. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት 2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

1. ወዴት፣ መቼ፣ ለምን እንደተጻፈች
2. የመልእክቱ እውነተኛነት

### ምዕራፍ 5. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች

1. ሀገሯ
2. መቼ፣ ወዴት፣ ለምን እንደተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

### ምዕራፍ 6. በመጀመሪያ የእሥራት ጊዜው በጳውሎስ የተጻፈ

1. ወዴት መቼ ለምን እንደተጻፈች

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ 7. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

1. የመልእክቱ ተቀባዮች
2. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን
3. መቼ ወዴት ስለምን ተጻፈች
4. የመልእክቱ እውነተኛነት

ምዕራፍ 8. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

1. ሀገሩ
2. መቼ፣ ወዴት፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

ምዕራፍ 9. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት 1 ወደ ቆላስይስ ሰዎች

1. ሀገሩ
2. ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

ምዕራፍ 10. የጳውሎስ መልእክት 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

1. ሀገሩ
2. መቼ፣ ወዴት፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

ምዕራፍ 11. የቅዱስ ጳውሎስ 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ

1. ወዴት መቼ ስለምን ተጻፈች
2. የመልእክቱ እውነተኛነት

ምዕራፍ 12. የጠባቂነት መልእክት

1. የጳውሎስ መልእክት 1ኛ ጢሞቴዎስ
2. [illegible]
3. ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን ተጻፈች
4. የመልእክቱ እውነተኛነት

ምዕራፍ 13. 2ኛ ጢሞቴዎስ

1. መቼ ወዴት፣ ስለምን ተጻፈች
2. የመልእክቱ እውነተኛነት

www.ethiopianorthodox.org

**ምዕራፍ 14. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ**

1. ሰውየው
2. ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት
4. የጠባቂነት መልእክቶች

**ምዕራፍ 15. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደፊልሞና**

1. ሰውየው
2. ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

**ምዕራፍ 16. የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን**

1. ሰዎች
2. ጸሐፊው
3. ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን ጻፈ

**ምዕራፍ 17. የያዕቆብ መልእክት**

1. ጸሐፊው
2. መቼ፣ ወዴት፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቱ እውነተኛነት

**ምዕራፍ 18. የጴጥሮስ መልእክት**

1. ጸሐፊውና የተላከላቸው ሰዎች

ሀ. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ

1. የመልእክቱ እውነተኛነት

ለ. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ

**ምዕራፍ 19. የዮሐንስ መልእክታት**

1. ጸሐፊው
2. የተላከላቸው ሰዎች
3. ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን እንደተጻፈች
4. የመልእክቱ እውነተኛነት

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ የዮሐንስ መልእክት 2ኛ

1. ጸሐፊው የተላከላቸው
2. መቼ፣ የት፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቲቱ እውነተኛነት

ሐ/ የዮሐንስ መልእክት 3ኛ

1. ጸሐፊውና የተላከላቸው
2. የት፣ መቼ፣ ስለምን ተጻፈች
3. የመልእክቲቱ እውነተኛነት

## ምዕራፍ 20. የይሁዳ መልእክት

1. ጸሐፊውና የተላከላቸው ሰዎች
2. የት፣ መቼ፣ ስለምን እንደተጻፈች
3. የመልእክቷ እውነተኛነት

## ምዕራፍ 21 ራእየ ዮሐንስ

1. ጸሐፊው
2. የትርጉሙ ስልት
3. የመጽሐፉ እውነተኛነት

www.ethiopianorthodox.org

2ኛ. የመሸሸፋ መንፈሳዊነትን፣ ራሱን በመሰ ይዘት በእግዚአብሔር መንፈስ መሻፋን የሚያመለክት ቢሆን፣ በዚህን ጊዜ አንሰዴና የጦሽት ሰራ የተሸከሙት/የበሽደኒ/ መጻ..ፍት ከቀኖና ውጭ እንዲሆኑ ቤተ ክርስቲያን ይበቀችበችው፡፡ ሮክንያተሮ በሙስብችው የሚገኘው ሰው ሠራሽ /ተርታ ነገር/ መገኘት ነበር፡፡

3ኛ. የጠቅላላ ተቀባይነትን፣ በዓለም ያሉ ትገኘው በበታ ተከፋፍለ በአምነትና በትምህርት ግን አንድ የሆኑችው ቤተ ክርስቲያን ያለ መለያየት ቀኖና የሆነውን በሙበታቸው ተስማምተ ስለተቀበለችው፣ አንዳንዱ በየጊዜው ፍኖት ያላደረጉትና ያልመረመሩ ቤተ ክርስቲያኖች ቀድሞ ሲለው ተቀብለናቸው የነበረትን የሰብት ፲ ቆኖች እንደያዙ ቢቆዩም የበለጠው ክፍል አግኝቶ ጨለቸው፡፡ 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቢቻ ተቀበለችው፡፡ ከዚሁ በኋላ ግን ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ መርመር ያዘችና ንጹሕ ሆኖ ያገኘችው ሁሉ ጊ ስለሆነ ቅዱስ ቢሉ ትዳ ስ? አድርጋ ያዘችው፡፡

እነዚህን 3ቱን የመለያ ዘዴዎች ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጊዜ የም ስነችው አልነበረም፡፡ ሲለ ስርዓትን በሰበ ያደረገችው አልነበረም፡፡ በአንድ ጊዜ የሆነና የተፈጸመ ነገር አልነበረም፣ የዚህ ከጭንት እስከ ጥጨ ግን ረዙ ጊዜ ፈጅቷል፡፡

አቢሲኒቱ ወንጌል የተባለ ይገኛል፣ እነዚህ አቢሲኒቱ የተባሉት ሕዝቦች አይሁዳዊያን መናንያን የተለየና ሥርዓት ያላቸው ነበሩ፣ ክርስትናን ይቀበሉ እንጂ የክርስትናው የተለየ አስተያየት ነበራቸው፣ ለምሳሌ 1ኛው ወገን ክርስቲያን ሆኖ የዕብራዊያንን ሥርዓት አጥብቆ ይጠብቅ ነበር፣ ሌላው ወገን ደግሞ የግሪክን ፍልስፍና ይዞ ከፍልስፍናው ጋር የሚስማማ ወንጌል ነበረው፡፡ እንዲሁም ሌሎች የሐዲስ ኪዳን አፖክሪፋዎች በተለያዩ መልክ ይገኛሉ፣ በዚሁ ሐዋርያት በሐሰት ስም የተጻፉ

ለምሳሌ፡—

1. የጴጥሮስ ዜና
2. የዮሐንስ "
3. የኒቆዲሞስ "
4. የእንድርያስ ዜና
5. የቶማስ "
6. የሌሎችም የሐዋርያት ስራዎች ራዕዮች በብዛት ይገኛሉ፡፡
   ይህን ከመሰብሰብ አልፈን አልባሌ ራዕዮ የሐዲስ ኪዳን
   መጻሕፍትን ይዞ ወጥቶ ቀኖናነትን ይዞ ይገኛሉ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ግሪክኛው ከተለመደው ግሪክኛ በቃላትና በዓረፍተ ነገር አሠራሩ፣ በአስተሳሰቡ ባይቀር ትንሽ ለየት ያለ አገላለጥ ይገኝበት ነበርና፣ እስክንድሪያዊ ቋንቋ ያሰኘው እስክንድር በተስፋፋበት አገር ሁሉ ግሪክኛው ሲነገር ከየሀገሩ ቋንቋ ጋር እየደበለቀ ጥሩ በዚያው አገር ስሜት ግሪክኛውን ለሚናገሩት ከጥንቱ ግሪክኛ የተለየ መሆኑን ለመግለጥ ነው::

የቅዱስ መጽሐፍ ቋንቋ የተባለበት ዋነኛ በመሆኑ ሐዲስ ኪዳን በዚህ ዓይነት ቋንቋ የተጻፈ በመሆኑና በተለይ ቋንቋውን የሚያንፀባርቀው ቅዱስ መጽሐፍ ነውና::

ብዙ ቴዎሎጂያን እንደሚሉት ግን ስሙ ግሪክኛ ነው እንጂ ሐዲስ ኪዳን የተጻፈበት ዲያሌክት ቅዱስ መንፈስ የገለጠው ሐዲስ የቅዱስ መጽሐፍ ቋንቋ ነው ይላሉ::

www.ethiopianorthodox.org